በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን በግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት የክትትል ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2009

አዲስ አበባ

ማውጫ

ማውጫ i
ክፍል አንድ 1
መግቢያ 1
የክትትል ኦዲቱ ዓላማ 2
የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 2
የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 2
ክፍል ሁለት 3
በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣ 3
ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎችን ለመከታተል በዕቅድ መያዙን በተመለከተ፡- 3
የህክምና ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ መመሪያዎች የወጡና ለጤና ተቋማት የደረሱ መሆኑን በተመለከተ፡- 4
በጤና ተቋማት ለሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞችና ሌሎች ባለሙያዎች የሚሰጡ ስልጠናዎችን በተመለከተ፣- 5
ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የቆሻሻ ማቃጠያ/ኢንስሌሬተር/ ደረጃውን ጠብቀው የተሰሩ መሆናቸውን በተመለከተ፣ 6
ለቆሻሻ ማስወገጃ የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች በጤና ተቋማት መሟላታቸውን በተመለከተ፣ 7
በግል የጤና ተቋማት እና በጤና ቢሮዎች መካከል ስላለው የመረጃ ልውውጥ በተመለከተ፡- 8
የህክምና ቆሻሻን ለማስወገድ በግል የጤና ተቋማት ባለሙያ የተመደበ መሆኑን በተመለከተ 9
ከህክምና ተቋሙ የሚወጡ ቆሻሻዎች ከጤና ተቋሙ ከመውጣታቸው በፊት የብክለት ደረጃቸውን እንዲቀንሱ ተደርገው የሚወጡ መሆኑን በተመለከተ፣ 10
የህክምና ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበት ሁኔታ መኖሩን በተመለከተ፣ 11
ክፍል ሦስት 13
የመደሚደሚያ ሀሳብ (CONCULUSION) 13
3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው 13
3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸውና መሻሻል ያልታየባቸው 13
ክፍል አራት 16
የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation) 16

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. ሀገራችን ኢትዮጵያ በሁሉም የስራ መስክ ብቁ የሆነና ምርታማ ዜጋን ለማፍራት የህብረተሰቡንም ሆነ የእንስሳቱን ጤና የተሟላ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የጤና አገልግሎት ዕድገት ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት አስፈላጊ ከሆኑ ጥልቅ ግብዓቶች አንዱ ነው፡፡

2. የጤና ችግር በመሠረታዊ የጤና ክብካቤ የሕዝቡን ስነልቦናዊ አመለካከት በመለወጥ ሊፈታ እንደሚችል በመታመኑ ህብረተሰቡ በየደረጃው ጤናውን እንዲጠብቅና የወደፊቱም ትውልድ ጤናው ተጠብቆ ኃላፊነቱን እንዲረከብ ለማስቻል የጤና አጠባበቅ ህግ በማስፈለጉ በአዋጅ ቁጥር 200/1992 የህዝብ ጤና አጠባበቅ በአገሪቷ የጤና ፖሊሲ የአካባቢ ደህንነት መጠበቅ እንዳለበት፣ ከሆስፒታል የሚወጡ ደረቅ፣ፍሳሽ ወይም ሌሎች ቆሻሻዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝ እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡

3. የአካባቢ ጤና አገልግሎት ሥራን ተፈጻሚ ለማድረግ ኃላፊነቱ በመጀመሪያ በጤና ጥበቃ ሚኒስትር የሃይጂንና አካባቢ ጤና አገልግሎት መምሪያ ሲሆን አሁን ግን በአዋጅ ቁጥር 661/2002 ለተቋቋመው ለኢትዮጵያ የምግብ፣ መድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን ተሰጥቷል፡፡

4. በየትኛውም የዓለም አገራት (ባደጉትም ሆነ በማደግ ላይ ባሉት) የቆሻሻ አስተዳደር ሥራ የሰውና የእንስሳትን ጤና ለመጠበቅና የአካባቢ ጥበቃን ዕውን ለማድረግ ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ ይገኛል፡፡ የጤና ተቋማት ማለት የምርመራና ሕክምና፣ የጤና ምርመራ፣ የማይክሮ ባዮሎጂካል፣ የኬሚካል፣ የቶክሲኮሎጂካል ምርመራ ሥራ የሚካሄዱባቸውን ድርጅቶችን ያጠቃልላል፡፡ የጤና ተቋማት ቆሻሻ የሚፈረጀው አደገኛነት ባላቸው ቆሻሻዎች (hazardous waste) ውስጥ ሲሆን፣ ይህም ከሰውና ከእንስሳት በሽታ ጋር የተጣመረ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ቆሻሻ የሚያካትታቸው መድኃኒቶች፣ ሹልና ስለት ያላቸው ነገሮች (መርፌ፣ ሲሪንጅ፣ ምላጭ …)፣ ቁስል የታሸገባቸው ፋሻዎች፣ ከሰውነት የሚወጡ ፈሳሾችና የሰውነት አካላት (ደም፣ የደም ተዋጽኦ፣ ተቆርጦ የሚቀር የሰውነት ክፍል፣ ብልቶች) ሲሆኑ እነዚህም የቫይረስ፣ የባክቴሪያና ጥገኛ የሆኑትን የበሽታ ዘሮችን የሚይዙ በመሆኑ በትክክሉና በጥንቃቄ ካልተያዙና ካልተወገዱ አደገኛ በሽታዎችን ሊያሰራጩ የሚችሉ ናቸው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

5. በግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አስመልክቶ ተከናውኖ በነበረው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ በተገለጹ ግኝቶች እና በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን እንዲሁም የሚመለከታቸው ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች (የኢትዮጵያ የምግብ ፣መድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን) ተገቢውን የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋታቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

6. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው የኢትዮጵያ የምግብ፣ መድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር የሥራ ሂደት እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በአዲስ አበባ ከተማና በአሮሚያ ክልላዊ መንግስት ሠላሳ የግል ጤና ተቋማት ውስጥ አስራ ስምንት የግል የጤና ተቋማት ታይተዋል፡፡ በተጨማሪም በክዋኔ ኦዲት ግኝቶችና በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎት በኦዲቱ ወቅት ከነበረው የአሰራር ክፍተት የተስተካከለ መሆኑን ለማረጋገጥ የተለያዩ የአፈፃፀም መረጃዎችን በመከለስ፣ ለየግል የጤና ተቋማቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች ቃለ መጠይቆችን በማቅረብና የቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ ማጓጓዣ እና ማቃጠያ ሥፍራዎችን በቦታውን በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ ነው፡፡

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

7. ክትትል ኦዲቱን ለማከነወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣

ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎችን ለመከታተል በዕቅድ መያዙን በተመለከተ፡-

8. የግል የጤና ተቋማትን የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ለመቆጣጠር ባለስልጣን መ/ቤቱ በ2003 ዓ.ም እና በ2004 ዓ.ም ዕቅድ ያልያዘ መሆኑ፣ የክልል ጤና ቢሮዎችም /አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ፣ ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ ቁጥጥር ለማድረግ ዕቅድ ቢይዙም በዕቅዱ መሰረት ያልተሰራ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቆ ነበር፡፡

9. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ በስሩ ባሉና ፍቃድ በሚሰጣቸው የግል የጤና ተቋማት የህክምና ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ዕቅድ በማዘጋጀት፣ በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየትና የትብብር ስልት በመንደፍ መሰራታቸውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚገባ መሆኑን እንዲሁም የክልል ጤና ቢሮዎችም ሆኑ የከተማ ጤና ጽ/ቤቶች የቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን በተያዘላቸው ጊዜ መከናወኑን ተገቢውን የአቅም ግንባታ ሥራ በመስራት ሊተገብሩ የሚገባ መሆኑን በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

10. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ በተላከው የድርግት መረሃ-ግብር ላይም የተጠቀሰው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከክልል ተቆጣጣሪ አካላት ጋር በ2006 በጀት ዓመት በ6 ወር እቅድ አፈፃፀም ግምገማ ላይ ውይይት ተደርጎበት በሁለተኛው 6 ወር እቅድ ወስጥ ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ አካተው እንዲያቅዱ ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑን ተገልፀዋል፡፡

11. በዚህም መሠረት ባለሥልጣን መ/ቤቱ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ ባለሥልጣን እና የኦሮሚያ የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችን ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ወሳኝ የሥራ ሂደት በ2007፣ በ2008 እና በ2009 በጀት አመት

በእቅዳቸው ወስጥ አካቶ በማቀድ በእቅዱ መሠረት ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ተረጋግጧል

የህክምና ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ መመሪያዎች የወጡና ለጤና ተቋማት የደረሱ መሆኑን በተመለከተ፡-

12. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተዘጋጀ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ቢኖርም በናሙና ተመርጠው የታዩ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልል ለሚገኙ 42 የግል የጤና ተቋማት በሙሉ መመሪያው ያልደረሳቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቆ ነበር፡፡

13. በመሆኑም ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በአግባቡ ካልተያዙና ካልተወገዱ የሚያደርሱት አደጋ ከፍተኛ በመሆኑ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ እየተዘጋጀ ያለው መመሪያ ተጠናቆ በማውጣትና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ለጤና ተቋማት ሊደርስ እና ስራ ላይ ሊውል የሚገባ መሆኑንና መመሪያው ለጤና ተቋማት መድረሱንና ስራ ላይ መዋሉን ባለስልጣን መ/ቤቱ ሊከታተልና ሊቆጣጠር የሚገባ መሆኑን በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

14. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የምግብ፣ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡በድርጊት መረሃ-ግብሩም ላይ የተገለፀው የመድኃኒት ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ለሚመለከታቸው አካላት የማሰራጨትና የማስተዋወቅ ሥራ የተሠራ መሆኑን፣ የሌሎች ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ መመሪያ በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ (በዌብ ሣይት) ላይ እንዲለቀቅ የተደረገ መሆኑን እና በቀረበው የኦዲት ሪፖርት መሠረት ከክልል ተቆጣጣሪ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ሥራው በቀጣይ እንዲከናወን አቅጣጫ የተሰጠ መሆኑን ተገልፀዋል፡፡

15. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በላከው የድርግት መረሃ-ግብር ላይ መመሪያ ተዘጋጅተው ለሁሉም የጤና ተቋማት የማሰራጨት ሥራ ተከናውኗል ብሎ የገለፁ ቢሆንም በክትትሉ ወቅት ለማረጋገጥ የተቻለው በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጀ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ የሌለ መሆኑን፣ ነገር ግን የሆስፒታሎች ስታንደርድ (Comprehensive Specilaizede Hosiptal Requirements Ethiopian standard) የሚል ተዘጋጅቶ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የጤና ተቋማት በቁጥር ተቆጥሮ በብዛታቸው ልክ ተባዝቶ ለሁሉም ክልሎች የተሰራጨ

መሆኑን፣ ሆኖም ግን ለግል የጤና ተቋማት ያልደረሰበት ምክንያት የወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች ችግር ሊሆን እንደሚችል የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

በጤና ተቋማት ለሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞችና ሌሎች ባለሙያዎች የሚሰጡ ስልጠናዎችን በተመለከተ፣-

16. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞችና ሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተከታታይነት ባለው መልኩ የማይሰጣቸው ሲሆን በፅዳት ስራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች ሥራቸውን የሚሰሩት ሲቀጠሩ በቃል በተሰጣቸው ኦሬንቴሽን ብቻ መሆኑን በኦዲት ግኝቱ ታውቆ ነበር፡፡

17. በመሆኑም በግል የጤና ተቋማት ለሚሰሩ የፅዳትም ሆነ በሌላ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ አወጋገድና በአካባቢ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ በተመለከተ በጤና ተቋማቱ፣ በጤና ቢሮዎች እና በባለስልጣን መ/ቤቱ ስልጠናዎች ሊያዘጋጁና ሊሰጡ የሚገባ መሆኑንና ባለስልጣን መ/ቤቱ የግል የጤና ተቋማት ሠራተኞች ስልጠና ማግኘታቸውንና በስልጠናው መሰረት መስራታቸውን ክትትል ሊያደርግ የሚገባ መሆኑን በኦዲቱ የማሻሻ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

18. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ በድርጊት መረሃ-ግብሩም የተገለፀው በ5 ሆስፒታሎች መመሪያውን ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትል ተደርጎ ባላደረጉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተሰጥተው እንዲሰሩ አቅጣጫ የተቀመጠ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

19. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው የክትትል ኦዲት በተደረገባቸው በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ
    - አዳማ ጄኔራል ሆስፒታል፣ ዮርዳኖስ ሀስፒታል፣ ቤተ ዛታ አጠቃላይ ሆስፒታል፣ ተክለኃይማኖት አጠቃላይ ሆስፒታል፣ ድንበሯ የእናቶችና ህፃናት ህክምና ማዕከል እና ቪዥን የውስጥ ደዌ ልዩ ክሊኒክ በራሳቸው ሥልጠና ለፅዳትና አስተዳደር ሠራተኞች የሚሰጡ ሲሆን

- ሌሎች የጤና ተቋማት ግን ሲቀጠሩ ኦረንቴሽን ከመስጠት ውጭ ሥልጠና የማይሰጡ መሆኑን፣
- ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በባለሥልጣን መ/ቤቱም ለፅዳትና ለአስተዳደር ሠራተኞች ስለቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ በተቀናጀ መልኩ ሥልጠና የሚሰጥበት ምቹ ሁኔታ ያልተፈጠረ መሆኑን

ታውቋል፡፡

20. ስለጉዳዩ የባለሥልጣኑ መ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው ጤና ጥበቃ ሚኒስተር ባዘጋጀው CASH (Clean and Safe For Heleath) በሚል ኢንሼቲቭ ንቅናቄን መነሻ በማድረግ ከክልሎች ጋር የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ሠፋ ያለ ውይይት የተደረገበት መሆኑን ምናልበት ለፅዳትና አስተዳደር ሠራተኞች ሥልጠና ያልተሠጠበት ምክንያት በግል የጤና ተቋማት የሚንቴሽንና ሃይጅን ባለሙያ ባለመኖሩ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የቆሻሻ ማቃጠያ/ኢንስሌሬተር/ ደረጃውን ጠብቀው የተሰሩ መሆናቸውን በተመለከተ፣

21. በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ የግል የጤና ተቋማት ውስጥ የተሰሩት የቆሻሻ ማጠራቀሚያና ማቃጠያዎች ወጥነት የሌላቸው ማለትም አንዳንዶቹ ትልቅ፣ ትንሽ፣ በራቸው ጠባብ እና ቆሻሻን ለመገልበጥ የማይመቹ፣ የጪስ ማውጫቸው አጭርና ረዥም መሆናቸው፣ አንዳንዶቹ ኢንስሌተር ባለመሰራቱ በርሜል ቆርጠው የሚጠቀሙ መሆኑን እንዲሁም ህክምና ከሚሰጥበት ክፍል 30 ሜ ያልራቀና ቆሻሻው ከማቃጠያ ውጭ የሚቃጠሉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታይቶ ነበር፡፡

22. በመሆኑም ለሜዲካል ቆሻሻ ማቃጠያ የሚሰሩ ኢንስሌሬተሮች ወጥ የሆነ አሰራር /ደረጃ/ ሊኖራቸው ወይም በኤሌክትሪክ እና በነዳጅ ኃይል የሚሰሩ ኢንስሌሬተሮች ለቆሻሻ ማስወገድ ስራ ከፍተኛ ጠቀሜታ ስለሚኖራቸው እነዚህን መጠቀም እንዲቻል ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በተመጣጠነ ዋጋ የሚያገኙበት መንገድ ሊመቻች የሚገባ መሆኑን በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

23. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ በድርጊት መረሃግብሩ ላይም የተገለፀው በ5 ሆስፒታሎች ላይ ኢኒሲኒሬተር

መኖሩን ቁጥጥር ተካሂዶ ደረጃውን የጠበቀ ኢንሲኒሬተር እንዲኖራቸው ግብረ-መልስ የተሰጠ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

24. በክትትሉም ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተወስደው የታዩት 18 የግል የጤና ተቋማት ሁሉም ኢንስኒሬተር ያላቸው መሆናቸውን፣ ሁሉም በኢንሲኒሬተር ውስጥ ለሊት የሚያቃጥሉ ቢሆንም ከአዳማ ጀኔራል ሆስፒታል፣ አሰላ ሮሆቦት ሆስፒታል፣ ዶ/ር አሽብር ሱራፌል የእናቶችና ህፃናት ስፔሻሊቲ ሴንተር እና አሰላ መነሃሪያ ክልንክ በስተቀር አስራ አራቱ /14 ከህኪምና ክፍሎች 30 ሜትር ያራቁ በየህክምና ክፍሎች አጠገብ የተሠሩ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

25. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ አንድ አንድ የግል የጤና ተቋማት ባለሀብቶች በስታንዳርዱ ላይ ቅሬታ ያላቸው መኖራቸውን፤ ይኸውም ከቦታ ጥበት ጋር ተያይዘው መንግስት መሬት እንዲሰጣቸው ጥያቄ የሚያነሱ ሲሆን መንግስት ደግሞ መሬት በኢንቨስትመንት ወስደው በስታንዳርዱ መሠረት መስራት እንዳለባቸው ምላሽ እየሰጣቸው መሆኑን፣ ሌላው በኢንቬስትመንት ኤጀንሲውና በቴክንካል ባለሙያዎች መካከል ቅንጅታዊ አሠራር ባለመኖሩ ለሆስፒታሎች ግንባታ ተብሎ በኢንቨስትመንት የሚሰጠው መሬት በተግባር ለሆስፒታሎች የማይሆኑና ከስታንዳርዱ ጋር የሚቃረኑ መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡

ለቆሻሻ ማስወገጃ የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች በጤና ተቋማት መሟላታቸውን በተመለከተ፣

26. በኦዲቱ ወቅት በግል የጤና ተቋማት በናሙና በተመረጡ ሆስፒታሎችና ከፍተኛ ክሊኒኮች በተደረገው የመስክ ጉብኝት፡-በዮርዳኖስ ሆስፒታል የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎቹን ቀለም በመቀባት ለመጠቀም ቢጀምሩም ቀለሙ እየለቀቀ በመቸገራቸው በከለር/በቀለም/ እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን በዩርዳኖስ ሆስፒታል፣ ቤተዛታ ሆስፒታል እና ሰናይ ከፍተኛ ክሊኒክ አደገኛና በሽታን የሚያስተላልፉ የሚባሉ የቆሻሻ ዕቃዎች ላይ (infections waste) በማለት በፅሑፍ ፅፎ ዕቃዎቹ ላይ በመለጠፍ እየተጠቀሙ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት ታይቶ ነበር፡፡

27. በመሆኑም ከጤና ተቋማት ለሚወጡ ቆሻሻዎች ማጠራቀሚያ፣ ማጓጓዣና ማስወገጃ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ሊሟሉና በየክፍሉ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ የሚያገለግሉ ዕቃዎችም በከለር ተለይተው አገልግሎት ሊሰጡ የሚገባ መሆኑን፣ ይህም መሟላቱን ባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ የጤና ቢሮዎች ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ እንደሚገባ በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት

የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

28. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ውስጥ በዚህ ግኝት ዙሪያ የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ሁኔታን አስመልክቶ የተገለጸ ነገር የለም፡፡

29. በመሆኑም በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመረጠው የታዩት 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ በአብዘኛዎቹ የቆሻሻ ዕቃዎች ላይ (infections waste) በማለት በዕሑፍ ዕፎ ዕቃዎቹ ላይ በመለጠፍ እየተጠቀሙ በመሆኑ በኦዲት ግኝት ወቅት ከነበረው በተለየ በስታንዳርዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት በከለር በተለየ ዕቃ የማይጠቀሙ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

30. ይህንን በተመለከተ የግል የጤና ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች በስታንዳርዱ መሠረት ዕቃውን በከለር ለይተው ያልተጠቀሙበት ምክንያት ተጠይቀው የሠጡት ምላሽ በስታንዳርዱ ላይ የተቀመጠው ዕቃ በገበያ ላይ ለማግኘት የተቸገሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

31. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ በስታንዳርዱ ላይ የተቀመጠውን ሟሟላት ለገበያ ውድድርና ወደ ተሻለ ደረጃ ለማደግ የሚደረግ ጥረት በመሆኑ ሁሉም እንዲያሟሉ ግፊት የሚያደርጉ መሆኑን፤ ሆኖም ግን እንደ መሠረታዊ ችግር የሚያነሱት እቃው በገበያ ላይ ማግኘት አልቻልንም የሚል በመሆኑ በላስቲክ ውስጥ ፌስታልን በከለር ለይተው መጠቀም እንኳን ሲችሉ ባለመጠቀማቸው የአመለካከትም ችግር ስላለባቸውም ጭምር ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

በግል የጤና ተቋማት እና በጤና ቢሮዎች መካከል ስላለው የመረጃ ልውውጥ በተመለከተ፡-

32. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ ሆስፒታሎች፣ ከፍተኛ ክሊኒኮች እና መካከለኛ ክሊኒኮች የመስክ ስራ ወቅት በጤና ቢሮ የክትትል ስራ ስለመደረጉ ለማረጋገጫ እንዲሆን የቁጥጥር እና ክትትል ስራው ውጤት እና መስተካከል ስለሚገባቸው ነገሮች የሚገልፅ ግብረ-መልስ በጤና ቢሮዎች በኩል እንደማይሰጣቸው ከጤና ተቋማቱ ለማወቅ የተቻለ መሆኑን በተጨማሪም የግል ጤና ተቋማት የህክምና ቆሻሻን በተመለከተ የሚይዙትም ሆነ ለጤና ቢሮዎች የሚልኩት መረጃ እንደሌለ ለማወቅ ተችሎ ነበር፡፡

33. ባለስልጣኑ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ እና የክልል ጤና ቢሮዎች በስራቸው ካሉ ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎችን ቁጥጥርና ክትትልን በተመለከተ ተገቢው የመረጃ ልውውጥ

ሥርዓት በተጠናከረ ሁኔታ እንዲኖራቸው ክትትል ሊያደርግ የሚገባ መሆኑን ይህም የጤና ተቋማቱ ለቆሻሻ አያያዙና አወጋገዱ ትኩረት እንዲሰጡና እንዲሰሩ ሊያደርጋቸው የሚችል መሆኑን በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

34. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ውስጥ በዚህ ግኝት ዙሪያ የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ሁኔታን አስመልክቶ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ በተጨማሪም በክትትል ኦዲቱ ወቅት የታየው የቆሻሻ አያያዝና አወገገድን በተመለከተ የግል የጤና ተቋማት ከጤና ቢሮዎች እና ከተቆጣጣሪ አካላት ጋር ምንም አይነት የመረጃ ልውውጥ የሌላቸው መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

35. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ በአጠቃላይ በተቆጣጣሪ አካላት እና የጤና ተቋማት መካከል የመረጃ ልውውጥ ችግር ያለ መሆኑን፣ ጤና ቢሮዎች የህክምና አገልግሎት ሪፖርት ሲቀበሉ ምን ያህል የተበላሸ መድኃኒት እንዳለ እንኳን የማይጠይቁ መሆኑን፣ በዚህም የተነሳ ተቆጣጣሪ አካላት ከጤና ጽ/ቤቶች ተለይተው መውጣት አለባቸው ብሎ ጥረት የሚያደርጉ መሆኑንና ባለሥልጣን መ/ቤቱ በ5 ዓመት እቅድ ውስጥ የሥርዓት (System) ኦዲት ለማድረግ ዕቅድ ይዞ እየሠራ መሆኑና በሲስተም ኦዲትም ጥሩ የሆነ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የህክምና ቆሻሻን ለማስወገድ በግል የጤና ተቋማት ባለሙያ የተመደበ መሆኑን በተመለከተ

36. የጤና ተቋማት በስራቸው ማቋቋም ከሚገባቸው የስራ ክፍሎች ውስጥ የሳኒቴሽን እና ሃይጂን ባለሙያ አንዱ መሆኑን ተገልጿል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የግል የጤና ተቋማት ውስጥ የሳኒቴሽን እና የሃይጂን ባለሙያ በመቅጠር የህክምና ቆሻሻዎች በዚሁ ባለሙያ እንዲለዩ ያልተደረገ መሆኑን በተጨማሪም የህክምና ቆሻሻ የማፅዳት ስራ ተቀጥረው ለሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞች ስለሚሰሩት ስራ እንዲያውቁ በሚመለከተው የተቋሙ የሥራ ክፍል ተዘጋጅቶ የተሰጣቸው የስራ መዘርዝር አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሎ ነበር፡፡ በመሆኑም በግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ በኃላፊነት የሚሰራ ባለሙያ/ሳኒቴሪያል/ በሆስፒታሎችና በከፍተኛ ክሊኒኮች ሊሟሉ ይገባል፡፡ በፅዳት አገልግሎት ለተቀጠሩም ባለሞያዎች በተቋሞቹ የስራ መዘርዝር ተዘጋጅቶ ሊደርሳቸውና

ስለተግባራዊነቱም ተቋሙና የጤና ቢሮዎች ክትትል ሊያደርጉ የሚገባ መሆኑን በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር ፡፡ ይህንን የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

37. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ውስጥ በዚህ ግኝት ዙሪያ የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ሁኔታን አስመልክቶ የተገለጸ ነገር የለም፡፡

38. በተጨማሪም በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተወሰደው በታዩት 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ተክለሐይማኖት ሆስፒታል፣ ላንድማርክ ሆስፒታል፣ ቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል፣ በአዳማ ከተማ አዳማ ጄኔራል ሆስፒታል፣ አቅልሲያ መታሰቢያ ጠቅላላ ሆስፒታል እና ቤተዛታ አጠቃላይ ሆስፒታል በስተቀር 12ቱ የግል የጤና ተቋማት የሳንቴሽንና የሃይጅን ባለሙያ ቀጥረው በዚሁ ባለሙያ ቆሻሻ እንዲለይ ያላደረጉ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

39. ይህንን በተመለከተ የግል የጤና ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሳንቴሽንና ሃይጅን ሙያ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በገበያ ላይ ለማግኘት ያልቻሉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ የባለሥልጠና መ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ደግሞ የሳንቴሽንና የሃይጅን ባለሙያ በሁሉም የጤና ተቋማት ሊኖር የሚገባ በመሆኑን የሰው ሀይሉን በገበያ ላይ ማግኘት አልቻልንም የሚሉ የጤና ተቋማት የኢንቫሮመንቱ ሥራ ከነርሶች መካከል ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግ በዚህ ባለሙያ እንዲሠራ ማድረግ የሚችሉ መሆኑን ጭምር ገልፀው እንደአጠቃላይ ሲታይ በዚህ ሙያ የሠለጠኑ የሰው ኃይል በገበያ ላይ በስፋት ለማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑም መንግስት በመስኩ የትምህርት ዝግጅት ቢያዘጋጅ የተሻለ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

ከህክምና ተቋሙ የሚወጡ ቆሻሻዎች ከጤና ተቋሙ ከመውጣታቸው በፊት የብክለት ደረጃቸውን እንዲቀንሱ ተደርገው የሚወጡ መሆኑን በተመለከተ፣

40. በናሙና ተመርጠው ከታዩ ሆስፒታሎችና የጤና ተቋማት ውስጥ ከሶስቱ (በአዲስ አበባ በቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል እና በቤቴል ቲቺንግ ሆስፒታል፣ በአሰላ ከተማ ዶ/ር አሸብር ሱራፌል እስፔሻል ክሊኒክ) በስተቀር ከህክምና የሚወጡ ፍሳሾች የጉዳት መጠናቸው ሳይመረመር ወደ አካበቢው የሚለቀቁ መሆኑን ተገልፆ ነበር፡፡

41. በመሆኑም ከጤና ተቋማቱ የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎች የብክለት ደረጃቸው ሳይለካ እንዳይለቀቁ የባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ የጤና ቢሮዎች ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉና ለተቋማቱም ይህን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲያገኙና የልኬት መጠናቸውን ሳያስለኩ

እንዳይለቁ የሚደረግበት መንገድ ሊዘረጋ የሚገባ መሆኑን በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

42. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ውስጥ በዚህ ግኝት ዙሪያ የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ሁኔታን አስመልክቶ የተገለጸ ነገር የለም፡፡

43. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተወስደው ከታዩት 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ በኦሮሚያ ክልል አሰላ ከተማ ዶ/ር አሸብር ሱራፌል የእናቶችና የህፃናት ስፔሻሊቲ ሴንተር ከህክምና ክፍል ሽንት ቤቶች የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎችን ለባዮ ጋዝ እንዲውል በማድረግ እየተጠቀሙ ያሉ ሲሆን ከህክምና ክፍሎች የሚወጡ የሜዲካል ቆሻሻዎች የጉዳት ደረጃ ለማስለካት የሚያስችል ሥርዓት (system)ያዘጋጁ ሲሆን እስከ አሁን የማጠራቀሚያ ገንዳ ባለመሙላቱ አስለክተው ወደ አካባቢ ያለቀቁ መሆናቸው፣ ቀሪዎቹ አስራ ሰባት /17/ የግል የጤና ተቋማት ከህክምና ክፍሎች የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎች በሴፍቲ ታንከር በማጠራቀም ሲሞላ የሚያስመጥጡ በመሆኑ በሁሉም በናና በታዩት ተቋማት ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ፈሳሽ ቆሻሻ የሌላቸው መሆኑን በመስክ እይታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የህክምና ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበት ሁኔታ መኖሩን በተመለከተ፣

44. በናሙና ተመርጠው በታዩ የጤና ተቋማት እንደተገለፀው ከህክምና ተቋሙ የሚወጡ ቆሻሻዎች ከተቃጠሉ በኋላ አመዱ ከሌሎች ቆሻሻዎች ማለትም የሜዲካል ቆሻሻ ካልሆኑ ቆሻሻዎች ጋር ተደባልቀው ቆሻሻ ለሚያጓጉዙ አካላት በመስጠት የሚደፉ መሆኑን፣ አመዱ ከህክምና ተቋሙ ውጭ በሚደፋበት ጊዜ የሚደፋበት ቦታ ማዘጋጃ ቤቱ ለደረቅ ቆሻሻ ባዘጋጀው ቦታ ላይ በመሆኑ ይሄም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ሊደርሱበት የሚችሉበትና የህክምና ቆሻሻዎች የተቃጠሉበት የሙቀት መጠን እና አመዱ ሊያመጣ የሚችለው የብክለት መጠን ስለማይታወቅ ለብቻው የማይቀበር መሆኑ፣ በኦዲት ወቅት ታይቶ ነበር፡፡

45. በመሆኑም ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በአግባቡ ለመያዝና ለማስወገድ፣ በጤና ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት ለመጠበቅ የጤና ቢሮዎች ከማዘጋጃ ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በአንድ ላይ የሚሆኑበትና የሚወገዱበት መንገድ ሊመቻች የሚገባ መሆኑን በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

46. በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

47. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በ2007 በጀት ዓመት በ4ኛ ሩብ ዓመት ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ለማድረግ እቅድ የያዙ መሆናቸውን የሚገልፅ የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

48. ይሁን እንጅ በተላከው የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት ከሚመለከታቸው የአዲስ አበባ ሆነ የክልል ከተሞች ማዘጋጃ ቤቶች እና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ያላደረጉ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የህክምና ቆሻሻ ሥርዓት ባለበት ሁኔታ የሚወገድበት ቦታ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ክፍል ሦስት

የመደሚደሚያ ሀሳብ (CONCULUSION)

49. የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን የሚከናወኑ ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናውኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላከ ቢሆንም የድርጊት መርሃ ግብር ያልወጣላቸው ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች መኖራቸው፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ ባለሥልጣን እና የኦሮሚያ የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችን ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ወሳኝ የሥራ ሂደት በ2007፣ በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በእቅዳቸው ወስጥ አካቶ በማቀድ በእቅዱ መሠረት ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን፣
- በናሙና የታዩት የግል የጤና ተቋማት ከህክምና ክፍሎች የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎች በሴፍቲ ታንከር በማጠራቀም ስሞላ የሚያስመጥጡ በመሆኑ የታዩት ተቋማት በሙሉ ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ፈሳሽ ቆሻሻ የሌለ መሆኑን ፣

3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸውና መሻሻል ያልታየባቸው

- የምግብ፣ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የህክምና ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ለሚመለከተው አካላት ያሰራጩበትና ያስተዋወቁበትን ጊዜ የሚያመለክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላኩ ቢሆንም፡-
  - በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጀ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ የሌለ መሆኑን፤
  - ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የጤና ተቋማት በቁጥር ተቆጥሮ በብዛታቸው ልክ ተዘጋጅተው ለሁሉም ክልሎች የተሰራጫ የሆስፒታሎች ስታንደርድ (Comprehensive

Specilaizede Hosiptal Requirements Ethiopian standard) ያለ ቢሆንም ለግል የጤና ተቋማት ያልደረሱ መሆኑን፤

- የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ ለፅዳትና አስተዳደር ሠራተኞች ሥልጠና ሥለመሰጠቱ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የድርግት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላኩ ቢሆንም፡
  - በናሙና ተመርጠው የክትትል ኦዲት በተደረገባቸው በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ከስድስቱ /6/ በስተቀር አስራ ሁለት/12/ ተቋማት ሲቀጠሩ ኦረንቴሽን ከመስጠት ወጭ በራሳቸው ሥልጠና ለፅዳትና አስተዳደር ሠራተኞች የማይሰጡ መሆኑን፣
  - በባለሥልጣን መ/ቤቱም ለፅዳትና ለአስተዳደር ሠራተኞች ስለቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ በተቀናጀ መልኩ ሥልጠና ስለመሰጠቱ ክትትልና ቁጥጥር ያልተደረገ መሆኑን፣
- የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የቆሻሻ ማቃጠያ/ኢንስሌሬተር/ ደረጃውን ጠብቀው የተሰሩ መሆናቸውን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላከ ቢሆንም፡-
  - በክትትሉ ወቅት በናሙና ተወሰደው ከታዩት 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ከአዳማ ጀኔራል ሆስፒታል፣ አሰላ ሮሆቦት ሀስፒታል፣ ዶ/ር አሸብር ሱራፌል የእናቶችና ህፃናት ስፔሻሊቲ ሴንተር እና አሰላ መነሃሪያ ክልንክ በስተቀር አስራ አራቱ/14/ የጤና ተቋማት ለቆሻሻ ማቃጠያ የሚጠቀሙት ኢንስኒሬተር በስታንዳርዱ መሠረት የህክምና አገልግሎት ከሚሰጥበት ክፍሎች 30 ሜትር ያራቁ መሆኑን፣
  - ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለቆሻሻ ማስወገጃ የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች በጤና ተቋማት መሟላታቸውን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ያላቀረቡ መሆኑን፣
  - በናሙና ተመርጠው ከታዩት 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ስምንቱ/8/ በከለር በተለየ ዕቃ የሚጠቀሙ ሲሆን አስሩ/10/ የቆሻሻ ዕቃዎች ላይ (infections waste) በማለት በፅሑፍ ፅፎ በመለጠፍ እየተጠቀሙ መሆኑን፣
  - የምግብ፣ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በግል የጤና ተቋማት እና በጤና ቢሮዎች መካከል ስላለው የመረጃ

ልውውጥ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለመስሪያ ቤታችን ያላቀረቡ መሆኑን፡፡

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት የታየው የቆሻሻ አያያዝና አወገገድን በተመለከተ የግል የጤና ተቋማት ከጤና ቢሮዎች እና ከተቆጣጣሪ አካላት ጋር ምንም አይነት የመረጃ ልውውጥ የሌላቸው መሆኑን፣
- የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የህክምና ቆሻሻን ለማስወገድ በግል የጤና ተቋማት የሣንቴሽንና ሃይጅን ባለሙያ መኖሩን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅተው ያልቀረቡ መሆኑን፣
- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተወሰደው በታዩት 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ከስድስቱ በስተቀር 12ቱ የግል የጤና ተቋማት የሳንቴሽንና የሃይጅን ባለሙያ ቀጥረው በዚሁ ባለሙያ ቆሻሻ እንዲለይ ያላደረጉ መሆኑን፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ከማዘጋጃ ቤቶእ እና ከሌሎች ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ለማድረግ በ2007 እቅድ የሚያሳይ የድርጊት መረሃ-ግብር ቢዘጋጁም ስለመከናወኑ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- በአገሪቱ ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ የህክምና ቆሻሻ የሚወገድበት ሥፍራ የሌለ መሆኑ፣

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

50. ከላይ በክፍል ሁለት ላይ የተጠቀሱ ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች በክፍል ሦስት ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ በተወሰኑት ግኝቶች የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል አለባቸው፡፡

51. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸው እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አሁንም የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም የድርጊት መርሃ ግብርም ለመ/ቤታችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ አለበት፡፡

52. በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ የኦሮሚያ ክልል እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን መ/ቤቶች እና በናሙና የታዩ የግል የጤና ተቋማት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡